
# Seminary West
# የደህንነት ማሻሻያዎች



# የፕሮጀክት የበስተጓላ ታሪክ

# የፕሮጀክት አካባቢ

- Seminary Road ከNorth Beauregard Street ወደ South George Mason Drive
- ያስታውሱ፣ ይህ ፕሮጀክት ከSeminary Road/North Beauregard Street መስቀለኛ መንገድ የማሻሻያዎች ፕሮጀክት ጋር እየተባበረ ነው።




# የበስተኋላ ታሪክ

- በከተማ አቀፍ የመኪና ግጭት ውሂብ ላይ በመመስረት፣ Seminary Road የከተማው ከፍተኛ የመኪና ግጭት ከሚደርስባቸው ኮሪደሮች አንዱ ነው።
- በእነዚህ ኮሪደሮስ ላይ 70% አካባቢ ጠቅላላ የሞት እና የከባድ ጉዳት የመኪና አደጋዎች የሚከሰቱ ሲሆን፣ ከአጠቃላይ የAlexandria መንገዶች 10% ያህል ይሸፍናል።
- የማህበረሰብ ነዋሪዎች በSeminary Road ላይ ስላሉ የደህንነት ችግሮች ስጋቶቻቸውን አሰምተዋል።
- በ2024፣ ከተማው  በSeminary Road ላይ የደህንነት ማሻሻያዎችን ለማጥናት ከMetropolitan Washington Council of Governments Regional Roadway Safety Program የቴክኒካል እገዛ ስጦታን አግኝቷል።



# የፕሮጀክት የጊዜ ሰሌዳ




# በአእምሮ መቀመጥ ያለባቸው እቅዶች




### Vision Zero የእርምጃ እቅድ

- እስከ 2028 ዜሮ ሞት እና ከባድ ጉዳቶች




### Alexandria የእንቅስቃሴ እቅድ

- ለብቻ ከመንዳት አማራጭ ለመምረጥ ለተጨማሪ ሰዎች ቀላል ማድረግ




### AlexWest የአነስተኛ አካባቢ እቅድ

- ለመልቲሞዳል ደህንነት፣ መዳረሻ እና ግንኙነት Seminary Roadን መገምገም
- የተጠቆመ ከመንገድ ውጪ የባለብዙ ጥቅም መንገድ

# ነባር ሁኔታዎች

- በእያንዳንዱ አቅጣጫ ሁለት የጉዞ መስመሮች
- ከፍተኛ ስፋት ያላቸው የጉዞ መስመሮች
- በአብዛኛው መስቀለኛ መንገዶች የመንገድ አካፋዮች ወይም የማዞሪያ መንገዶች የሉም
- ጠባብ የእግረኛ መንገዶች
- በርካታ የተሸከርካሪ መንገዶች
- ደካማ ወይም የተወሰኑ መሻገሪያዎች
- የተወሰኑ የአውቶብስ ማቆሚያ መገልገያዎች
- ደካማ የADA መዳረሻ






5223







DOVER




# ነባር ሁኔታዎች

## *የመኪና አደጋ አዝማሚያዎች (2018-2024)*

- **ከ150 በላይ ጠቅላላ የመኪና አደጋዎች**
  - በአማካይ በዓመት 22
- 2 የሞት አደጋዎች
  - ሁለቱ የእግረኛ አደጋዎች ነበሩ
- 7 ከባድ አደጋዎች፣ የሚያካትቱትም
  - የብስክሌት (2)
  - በአንግል(2)
  - የፊት (1)
  - የኋላ (1)
  - የአጋዘን (1)
- ግጭቶች መስቀለኛ መንገድ ላይ በዋነኝነት ተከስተዋል
- በርካታ ከመንገድ ውጪ በመውጣት የሚጋጩ አደጋዎች



# የተለመዱ የግጭት ገጽታዎች

- **ደህንነታቸው ያልተጠበቀ** የእግረኛ መሻገሪያዎች
- በሚታጠፍበት ጊዜ **ቅድሚያ መስጠት አለመቻል**
- ከውስጥ መስመር የግራ መታጠፊያዎች ጋር የተገናኙ **ድንገተኛ የመኪና መቆሞች**
- በቆሙ መኪናዎች ዙሪያ **እየተሽከረከሩ መዞር**
- ከምሽት ሰዓት፣ ከእክል፣ ከፍጥነት ወዘተ. ጋር የተገናኙ **ከመንገድ መውጣቶች**

# እኛ የሰማነው

*ኖቬምበር 2023*
*የማህበረሰብ ግብረመልስ ቅጽ (310 ምላሾች)*

**ቀዳሚ የሆኑ 3 ችግሮች**

- የመዞሪያ የመንገድ መስመሮች አለመኖር (61%)
- ከፍጥነት መጠን በላይ ማሽከርከር (60%)
- የእግረኛ ደህንነት (47%)


**የሚፈለጉ መስቀለኛ መንገድ ማሻሻያዎች**

- የቀይ መብራት ካሜራዎች
- የእግረኛ የደህንነት አያያዞች
- የመግቢያ መንገድ አያያዞች
- የተሻሻለ የመንገድ ምልክት

# እስካሁን የተሰራው

- ከ35 ማይል/ሰዓት ወደ 25 ማይል/ሰዓት የፍጥነት ወሰን መቀነስ
- የፍጥነት ራዳር ምልክቶች
- የፈጣን ግንባታ የትራፊክ ማረጋጊያ
- (ቀጣይ የሚመጣ) በFairbanks Avenue ያለ የትራፊክ ምልክት

# ምን ተቀየረ?




- በትንሹ ወደታች ያዘነበሉ ጠቅላላ የመኪና አደጋዎች
- በአብዛኛው በምዕራብ ወሰን አቅጣጫ ውስጥ በመሆን አነስተኛ የፍጥነት መቀነስ

# የፕሮጀክት ዓላማዎች

የትራፊክ ግጭቶችን መቀነስ

በሚያሽከረ ክሩ ሰዎች የትራፊክ መዘግየትን መቀነስ

ደህንነታቸ ው የተጠበቁ የጉዞ ፍጥነቶችን ማበረታታት

ለመራመድ ቀላል እና ደህንነታቸ ው የተጠበቁ ማድረግ

በብስክሌት ለመጋለብ ቀላል እና ደህንነታቸ ው የተጠበቁ ማድረግ

አውቶብስ ለመያዝ ቀላል እና ደህንነታቸ ው የተጠበቁ ማድረግ

በSeminary Road ላይ ማሽከርከር በበለጠ ስርዓት እና ተገማች ማድረግ

# የጎድፍ አማራጮች

# የንድፍ አማራጮች ማጠቃለያ

- የፕሮጀክት ቡድኑ በርካታ የፕሮጀክት አላማዎችን ለመሸፈን በርካታ የንድፍ አማራጮችን አጎልብቷል።
- ምንም አማራጭ ሁሉንም አላማዎች አልሸፈነም፣ ስለሆነም ልውውጦች ከግምት ውስጥ መግባት ያስፈልጋቸዋል።
- አማራጮች የሚያካትቱት ሁለቱንም የአጭር ጊዜ እና የረጅም ጊዜ ማሻሻያዎችን ነው።

# አማራጭ 1


## ይህ አማራጭ አሁናዊ ደረጃዎችን ለማሟላት የኮሪደር ክንውኖችን በማሻሻል የጉዞ መስመሮችን በማጥበብ እንደ ማዕከላዊ የመዞሪያ መንገድ መስመር አድርጎ ዳግም ጥቅም ላይ ያውላል።

### ጥቅሞች:-

- የማዕከላዊ መዞሪያ የመንገድ መስመር ወደግራ ለመዞር ቀላል ያደርገዋል እንዲሁም ወደ ግራ የሚዞሩ መኪኖች የሚመጡ የትራፊክ መታወኮችን ይቀንሳል።
- በአንድ አቅጣጫ ሁለት የመንገድ መስመሮችን መጠበቅ ከፍተኛ የመኪና መጨናነቅ በሚኖርበት ሰዓት የመኪና ፍሰት እንዲቀጥል ያደርጋል።
- ጠባብ የመንገድ መስመሮች ለእግረኛ መንገድ ከዋናው መንገድ መለያ አነስተኛ ርቀትን ያደርጋሉ።

### ከግምት የሚገቡ ነገሮች:-

- በፍጥነት ላይ አነስተኛ ተጽእኖ በአንዳንድ ሁኔታዎች ውስጥ፣ በፍጥነት ማሽከርከር በሁለት መስመሮች በአንድ አቅጣጫ ሊጨምር ይችላል።
- ለሚራመዱ፣ በብስክሌት ለሚጋልቡ ወይም አውቶብስ ለሚይዙ ሰዎች በከፍተኛ ሁኔታ አያሻሽልም።
- Seminary Road ትራፊክ ከአንዳንድ ተጨማሪ ሰልፎች ጋር በተወሰነ መስቀለኛ መንገድ እስከ ~25 ተጨማሪ የመዘግየት ሰከንዶች ሊታዩ ይችላሉ። ተጨማሪ መዘግየቶች ከፍተኛ መጨናነቅ ባለባቸው ሰዓታት አንዳንድ የመንገድ ዳሮች ሊጠበቁ ይችላሉ።



# አማራጭ 2

**ይህ አማራጭ ባዶ ቦታ እንዴት መንገድ ላይ ጥቅም ላይ እንደሚውል እና የመሃል መዞሪያ የመንገድ መስመርን ያቀርባል እንዲሁም የተጠበቀ የባለሁለት መንገድ የብስክሌት መስመርን ይጠብቃል።**

## ጥቅሞች

- የማዕከላዊ መዞሪያ የመንገድ መስመር ወደግራ ለመዞር ቀላል ያደርገዋል እንዲሁም ከግራ የሚዞሩ መኪኖች የሚመጡ የትራፊክ መታወኮችን ይቀንሳል።
- በሰሜን ጎን ያለው የእግረኛ መንገድ ከትራፊኩ እንደ ክፍተት በማድረግ በብስክሌት መጋለቢያ መስመሩ ይጠቀማል።
- አነስተኛ የጉዞ መስመሮች በእግረኛ መሻገሪያዎች ላይ ያለውን ደህንነት በከፍተኛ ደረጃ ያሻሽላል።
- ብስክሌት ለሚጋልቡ እና ስኩተር ለሚጠቀሙ ሰዎች የተሰጠ ቦታ የሚኖርረውን ደህንነት ያሻሽላል።

## ከግምት የሚገቡ ነገሮች

- Seminary Road ትራፊክ ከአንዳንድ ተጨማሪ ሰልፎች ጋር በተወሰነ መስቀለኛ መንገድ እስከ 37 ተጨማሪ የመዘግየት ሰከንዶች ሊታዩ ይችላሉ። ተጨማሪ መዘግየቶች ከፍተኛ መጨናነቅ ባለባቸው ሰዓታት አንዳንድ የመንገድ ዳሮች ሊጠበቁ ይችላሉ።
- በደቡብ ጎብ ያለው የእግረኛ መንገድ አልተሻሻለም



# አማራጭ 3

**ይህ አማራጭ ባዶ ቦታ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል እና የማዕከል መዞሪያ የመንገድ መስመርን ያቀርባል እንዲሁም የተጠበቀ የባለሁለት መንገድ የብስክሌት መስመርን ይጠብቃል።**

## ጥቅሞች

- የማዕከላዊ መዞሪያ የመንገድ መስመር ወደግራ ለመዞር ቀላል ያደርገዋል እንዲሁም ከግራ የሚዞሩ መኪኖች የሚመጡ የትራፊክ መታወኮችን ይቀንሳል።
- በሁለቱም ጎኖች ያሉ የእግረኛ መንገዶች ከትራፊኩ እንደ ክፍተት በማድረግ ከብስክሌት መጋለቢያ መስመሮች ሊጠቅም ይችላል።
- አነስተኛ የጉዞ መስመሮች በእግረኛ መሻገሪያዎች ላይ ያለውን ደህንነት በከፍተኛ ደረጃ ያሻሽላል።
- ብስክሌት ለሚጋልቡ እና ስኩተር ለሚጠቀሙ ሰዎች የተሰጠ ቦታ የሚኖርረውን ደህንነት ያሻሽላል።

## ከግምት የሚገቡ ነገሮች

- Seminary Road ትራፊክ ከአንዳንድ ተጨማሪ ሰልፎች ጋር በተወሰነ መስቀለኛ መንገድ እስከ 37 ተጨማሪ የመዘግየት ሰከንዶች ሊታዩ ይችላሉ። ተጨማሪ መዘግየቶች ከፍተኛ መጨናነቅ ባለባቸው ሰዓታት አንዳንድ የመንገድ ዳሮች ሊጠበቁ ይችላሉ።



# ከግምት ውስጥ የሚገቡ ሌሎች የኮሪደር አማራጮች

## የመንገድ ማስፋት

- ወጪ የሚከለክል
- በቅርብ ላሉ ንብረቶች ላይ ዋና ተጽዕኖዎች
- ለሚራመዱ፣ በብስክሌት ለሚጋልቡ ወይም አውቶብስ ለሚይዙ ሰዎች ትርጉም ባለው መልኩ ሁኔታዎችን አያሻሽልም።

## የሚመለሱ የመንገድ መስመሮች


- ለመቆጣጠር ከባድ/አሽከርካሪዎችን ግራ የሚያጋባ
- በሽግግር ጊዜያት ወቅት መዘግየቶችን ይፈጥራል
- ለሚያስፈልግ መሳሪያ የተወሰነ ቦታ የማይቻል ሊሆን ይችላል
- ሁኔታዎች ትርጉም በሚሰጥ ሁኔታ አያሻሽልም

## የመዞር ገደቦች

- ከሌሎች አያያዞች ጋር ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ሁኔታዎች በራሳቸው ትርጉም በሚሰጥ ሁኔታ አይሻሻሉም

# Seminary Road & South George Mason Drive

## በዚህ መስቀለኛ መንገድ ላይ ሊሆኑ የሚችሉ ማሻሻያዎች ሊያካትቱ የሚችሉት፡-



**የመታጠፊያ ማራዘሚያዎች**
ያጠሩ የመሻገሪያ ርቀቶች፤ ደህንነታቸው የተጠበቁ መዞሪያዎች




**የመንገድ መግቢያ አያያዞች**
ለአሽከርካሪዎች “እርስዎ ደህንነቱ ወደተጠበቀ ኮሪደር እየገቡ ነው” ይላል



**የእግረኛ መንገዶች**
ሰዎች የሚሻገሩበት የተመደበ ቦታ እንዲያገኙ ያደርጋል፤ በቦታው ላይ በመመስረት ምልክት የተደረገበት ወይም ያልተደረገበት ሊሆን ይችላል




**አደባባይ**
ትራፊክ እየተንቀሳቀሰ ደህንነታቸው የተጠበቁ የተሽከርካሪ ፍጥነቶችን እያበረታታል፤ ለውብ ማሻሻያዎች ያለ እድል

# የተገናኙ ፕሮጀክቶች

# Seminary Road & North Beauregard Street

በSeminary Road ላይ ከሌሎች ማሻሻያዎች ጋር በቅርበት እየተቀናጀ ያለ **የተናጠል ፕሮጀክት** አለ።

የተቀረጸው የAlexWest Small Area Plan ይህንን ከተሻሻለ የመንገድ ገጽታ ጋር በበለጠ የተጠቀጠቀ መስቀለኛ መንገድ አድርጎ ይወስዳል።




# በI-395 ቅርበት ላይ ያለ Seminary Road

እንደ West End High-Crash መስቀለኛ መንገዶች የኦዲት ፕሮጀክት እንደ ክፍል በመሆን **የተነጠለ ፕሮጀክት** አለ።

እነዚህ ፕሮጀክቶች በቅርብ ርቀት እየተቀናጁ ነው።

ለበለጠ መረጃ AlexandriaVA.gov/go/4794 ይጎብኙ።



# ቀጣይ እርምጃዎች

# በአጠቃላይ

በ Seminary Road ኮሪደር ውስጥ እየተከናወነ ያለ በርካታ ስራ እና ኢንቨስትመንት አለ!

ፍጹም የሚባሉ ምንም መፍትሔዎች የሉም፣ ነገር ግን **ነገሮችን የተሻለ ለማድረግ** ከእርስዎ ጋር መስራት እንፈልጋለን።



# የእርስዎን ግብረመልስ ያቅርቡ!

እስከ **ሜይ 19** የመስመር ላይ የግብረመልስ ቅጽን ያጠናቅቁ።

# ቀጣይ እርምጃዎች

የማህበረሰብ ግብረመልስ ይገምግሙ

ለተጨማሪ ጥናት ምክረሃሳቦች እና እድሎችን ያጎልብቱ

ለተጠቆሙ ለውጦች ሕዝባዊ ችሎት

# እናመሰግናለን!

ለበለጠ የፕሮጀክት መረጃ፣
የሚከተለውን ይጎብኙ፡-
AlexandriaVA.gov/go/6552